በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በኾነው፤

شَهْرُ رَمَضَانَ الَّذِى أُنزِلَ فِيهِ الْقُرْآنُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَاتٍ مِّنَ الْهُدَىٰ وَالْفُرْقَانِ

(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (እንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው::

(ሱረቱል በቀራ 2:185)

የረመዳን ዕቅዶች





አቡ ሁረይራ(ﷺ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ(ﷺ) እንዲህ አሉ

“ያ የተባረከው ረመዳን ወደ እናንተ በርግጥ መጥቷል፣ የላቀው አላህ ቀኑን እንድትፆሙ ግዴታ አድርጓል፣ በውስጡም የሰማይ ደጃፎች ይከፈታሉ፣ የእሳት በሮች ይዘጋሉ፣ ሰይጣኖችም ይቀፈደዳሉ፣ በውስጡም ከአንድ ሺ ወር ምትበልጥ ለሊት አለች፣ የሷን በረከት ያመለጠው በእርግጥ እሱ የተነፈገ ነው!”

[ሱነን አ-ነሳኢ]





አቡ ሁረይራ(ﷺ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ(ﷺ) እንዲህ አሉ

“የበላይና የላቀው አላህ እንዲህ አለ የአደም ልጅ ስራው ሁሉ ለራሱ ነው ፆም ሲቀር እሱ ለኔ ነው እኔም በሱ እከፍውለዋለሁ፤ ለፆመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት፤ አንደኛው ፆሙን ሲፈታ ሲሆን ሌላኛው ጌታውን ሲገናኝ በፆሙ ይደሰታል!”

[ቡኻሪ ዘግበውታል!]



የረመዳን አጀንዳ

የሶላት መከታተያ(ሱናህ)

ዒኢሻ(ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ(ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-

"አስራ ሁለት ረከዓ ሱናዎችን (ሶላት) የሰገደ ሰው አላህ በጀነት ውስጥ ቤት ይገነባለታል:- ከዙህር በፊት አራት ረከዓ፤ ከኋላው ሁለት ረከዓ፤ ከመግሪብ በኋላ ሁለት ረከዓ፤ ከኢሻ በኋላ ሁለት ረከዓ:: ከፈጅር በፊት ሁለት ረከዓህ" (ተርሚዚ)

ዓልይ(ረዐ) እንዳወሩት:- ነብየ(ﷺ) ከአስር ሶላት በፊት ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር::

(አቡድ ዳውድ)

የሶላት መከታተያ(ተራዊህ)

"ረመዳንን በእምነት እና ከአላህ ምንዳን ተስፋ አድርጎ በሱና ሰላቶች (ተራዊህ) የቆመ ሰው ያለፈው ወንጀል ይማርለታል::"

(ቡኻሪ ዘግበውታል)

የቁርአን መከታተያ

የሰላት ወቅትን ያማከሉ የተለያዩ መልካም ተግባራትን ያቅዱ ለምሳሌ:- በቀን ውስጥ ከሚሰገዱ የፈርድ ሰላቶች በፊት እና በኋላ ከቁርአን ገጾች አንድ ገጽ ማንበብ:: ይህም በቀን አንድ ጁዝ ይሆናል::

ዕለታዊ መገምገሚያ

የማለዳ እና የምሽት ውዳሴዎችን ለማግኘት:-
“ሒስኑል ሙስሊም” የተሰኘውን የአዝካር መጽሐፍ ይመልከቱ



“አላህ ዘንድ በጣም የተወደዱ ስራዎች ትንሽም ቢሆኑ ያለማቋረጥ የሚሠሩ ናቸው::”

(ቡኻሪ)







ዱዓ እና ሱናህ በረመዳን

በቴምር ወይም በውሃ ጾምን መፍታት

"ከናንተ አንዳችሁ የፆመ በተምር ይፍታው:: ተምር ባያገኝ በውሃ ይሰብረው ይህ የመንፃት መንገድ ነውና::" (ሱነን ኢብኑ ማጃህ)

ጾምን በማፍጠን መፍታት

"ሰዎች ጾምን ለመፍታት እስከ ቸኮሉ ድረስ በበጎ ነገር ላይ ይኖራሉ:: ጾምን ለማፍጠር ቸኩለ፤ አይሁዶች ያዘገዩታልና::" (ሱነን ኢብኑ ማጃህ)

ጾመኛ ሲያፈጠር የሚያደርገው ዱዓ

ذهب الظمأ وابتلت العروق وثبت الأجر إن شاء الله

"ጥሙ ተወገደ፤ ደም ሥሮች ረጠቡ፤ በአላህ ፍቃድ ምንዳው ተረጋገጠ"

(አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

اللهم إنك عفو تحب العفو فاعف عنا

አላህ ሆይ! አንተ ይቅርባይ ነህ፤ ይቅር ባይንትንም ትወዳለህ:: ይቅር በለን::

ይህንን ዱዓ አዘውትረው እንዲያነቡ ይመከራል፤ በተለይ በረመዳን የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በቀን እና በሌሊት::

ረመዳን 1

የዕለቱ አንቀጽ

ቀን | ወር | ቀን

አንድ ሰው ለምዕመን ወንዶች እና ሴቶች ምህረትን የለመነ እንደሆነ አላህ ለእርሱ በእያንዳንዱ ወንዴ ች እና ሴቶች ቁጥር መልካምን ይጽፍለታል::

(ጠበራኒ ዘግበውታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር:-

ጸማችንን እና መልካም ተግባራትን ስንፈጽም ከእየልኝ ስሜት እርቀን ኒያችንን ለአላህ ብቻ ጥርት እናድርግ:: ከአለቱ አንድ ወይም ሁለት ደቂቃዎችን ብቻ በመውሰድ ለምእመን ወንደች እና ሴቶች የአላህን ምህረት እንለምን::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጂድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



አንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

(ከ42-43 ያለውን ገጽ ይመልከቱ)

የዕለቱ ዱዓ:-

رَبَّنَا اغْفِرْ لِي وَلِوَالِدَيَّ وَلِلْمُؤْمِنِينَ يَوْمَ يَقُومُ الْحِسَابُ

«ጌታችን ሆይ! ለእኔም ለወላጆቼም ለምእመናንም ሁሉ ምርመራ በሚደረግበት ቀን ማር::»

(ሱረቱል ኢብራሂም 14:41)

ረመዳን 2

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ከቁርአን አንድ ፊደል አንኳ ያነበበ ሰው አንዲ ክዋኔው አንደ 10 ኽይር ስራ ይቆጠርለታል:: "አሊፍ ላም ሚም" አንድ ፊደል አይደለም "አሊፍ" ፊደል "ላም" ፊደል "ሚም" ፊደል ነው::

(ቲርሚዚ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ከሁሉም ሰላት በኃላ

ሱብሃነአላህ 33×
አልሃምዱሊላህ 33×
አላሁአክበር 33×
መጪረሻውን ላ ኢላህ ኢለሏህ ወሃደሁ ላ ሸሪከለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምድ ወሁዋ አላ ኩሉ ሸይኢን ቀዲር በማለት 100 መሙላት::
ይህንን ማለት ያለፉ ወንጀሎችን ያስምራል::
ወንጀሉ የባህር አረፋ ያህል ቢሆኑ እንኳ

(መስለም ዘግቦታል)

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


እንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

اللهم إنى أعوذ بك من الجبن وأعوذبك أن أرد إلى أرذل العمر وأعوذبك من فتنة الدنيا وأعوذبك من عذاب القبر

አላህ ሆይ! ከፈሪነት ባንተ እጠበቃለሁ! ወደ መጥፎ እድሜ መመለስንም ባንተ እጠበቃለሁ! ከዱኒያ ፈተናም ባንተ እጠበቃለሁ! ከቀብር ቅጣትም ባንተ እጠበቃለሁ!

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

ረመዳን 3

የዕለቱ አንቀጽ

ቀን | ወር | ቀን

ለአላህ መልካም ብድርን ብታበድሩ (ምንዳውን) ለናንተ ይደራርበዋል፤ ለናንተም ይምራል፤ አላህም አመስጋኝ ታጋሽ ነው።

(ሱረቱል ተጋቡን 64:17)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ለመስጂድ ግንባታ ለትምህርት ቤትም ኾነ ለማንኛውም የበጎ ስራዎች አቅምህ የቻለውን ለግስ። ያለህ/ሽ አቅም ጉልበት ከኾነ ደግሞ መስጂዶችን ማጽዳት የወላጅ አጦችን ቤት ማጽዳት እና ሌሎች ተግባሮች መከወን።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



አንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اَللَّهُمَّ إِنِّيْ أَعُوْذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ وَمِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ
وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ وَمِنْ شَرِّ فِتْنَةِ الْمَسِيْحِ الدَّجَّالِ

አላህ ሆይ! ከቀብር ቅጣትና ከጀሃነም ቅጣት ከህይወትና ከሞት ፈተና እንዲሁም ከአታላዩ መሲሕ አድ-ደጃል ፈተና በእንተ እጠበቃለሁ።

(ሙስሊም)

ረመዳን 4

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ለወንድሙ ከጀርባው (በሌለበት) የሚማፀን ሰው፤ የተሾመው መልአክ (ወደ ጌታው ልመናን ለመሸከም) እንዲህ ይላል:- አሚን ላንተም ነው::
(ሙስሊም)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ልብህን አጽዳ እና ዲዓ አድርግ ለምትወዳቸው ሰዎች መልካም ላደረጉልህም ለጎዱህም::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


እንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

(ከ42-43 ያለውን ገጽ ይመልከቱ)

የዕለቱ ዱዓ:-

رب تقبل توبتى واغسل جوبتى وأجب دعوتى وثبت حجتى واهد قلبى وسدد لسانى واسلل سخيمة قلبى

ጌታዬ ሆይ! መመለሴን ተቀበለኝ:: ወንጀሌን አፅዳልኝ:: ልመናዬን ተቀበለኝ መረጃዬን አፅናልኝ ልቤንም ምራት ምላሴን በእውነት አግራልኝ የልቤን ክፋት አስወግድልኝ::
(አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

ረመዳን 5

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

"እንድም ባሪያ በአላህ መንገድ ላይ አንድንም ቀን አይጾምም አላህ ፊቱን(አካሉን) የሰባ ዓመት የጉዞ ርቀት ያህል ከጀሃነም እሳት ያራቀው ቢሆን እንጂ::"

(ሙስሊም)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ለነዚያ ለሚፆሙት ወይም ምግብ ለሚፈልጉት ምግብ ወይም መጠጥ አቅርቡ (አዘጋጁ) በተምር ፍሬ ስባሪ እንኳን ቢሆን ከእሳት ተጠበቁ (ተጠንቀቁ)::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

እንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት እዝካር
- የምሽት እዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዊኔ
- ከእንቅልፍ በፊት እዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

الحمدلله الذى أطعمنى هذا الطعام ورزقنيه من غير حول منى ولا قوة

ያለኔ ጎያለና ብልሐት ይህንን ምግብ ለለገሰኝ አላህ ምስጋና ይገባው:: (ተርሚዚ ዘግቦታል)

ምግብ ከበላ በኋላ (ከላይ ያለውን) ያለ ሰው ያለፈው ጋጢአቱ ሁሉ ይሰረዝለታል:: (ተርሚዚ ዘግቦታል)

ረመዳን 6

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ከእናንተ የሚበልጠው በጣም ጥሩ ባህሪ ያለው ነው::

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ወላጆቻችሁን፣የትዳር አጋራችሁ፣ልጆቻችሁን፣ ወንድሞችና እህቶቻችሁን በእዝነትና ደግነት አስተናግዱ::

የአላህን ምሕረትና ይቅርታ አግኝተው ጀነተል ፊርደውስን እንደወፈቁ ዱዓም አድርጉላቸው::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



እንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم اهدنى لأحسن الأعمال وأحسن الأخلاق لا يهدى لأحسنها إلا أنت وقنى سيئ الأعمال وسيئ الأخلاق لا يقى سيئها إلا أنت

አላህ ሆይ! ወደ ጥሩ መልካም ስራና ወደ ጥሩ ስነ ምግባር ምራኝ:: ለዛች ጥሩ ለሆነች መልካም ስራና ባህሪ ከአንተ ውጪ የሚመራ የለም:: ከአንተ ውጪ ከመጥፎ ስራና ስነ ምግባር የሚጠብቅ የለምና::

ረመዳን 7

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

> አላህ ዘንድ በጣም የተወደዱ ሰዎች ለሰዎች በጣም ጥሩ የሆኑት ናቸው::
> (አህመድ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

በዲንያ እና አኼራ ጠቃሚ ይሆናሉ ብለው የሚያስቡትን መረጃዎች ወይም ቪዲዮች፤ ቁርኣን እና ሱናን "የአዕቱን ዲዓ" ሼር በማድረግ ያካፍሉ::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

- አንቀጽ
- ሱራ
- ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዲዓ:-

رَبِّ أَوْزِعْنِي أَنْ أَشْكُرَ نِعْمَتَكَ الَّتِي أَنْعَمْتَ عَلَيَّ وَعَلَىٰ وَالِدَيَّ وَأَنْ أَعْمَلَ صَالِحًا تَرْضَاهُ وَأَدْخِلْنِي بِرَحْمَتِكَ فِي عِبَادِكَ الصَّالِحِينَ

«ጌታዬ ሆይ! ያቺን በእኔና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ጸጋህን እንዳመሰግን የምትወደውንም በጎ ሥራ እንድሠራ ምራኝ:: በችሮታህም በመልካሞቹ ባሮችህ ውስጥ አግባኝ» (ሱረቱል ነምል 27:19)

ረመዳን 8

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

> የቂያማ ቀን ለእኔ ቅርብ ወዳጅ የሚሆኑት በእኔ ላይ ብዙ ሰለዋትን ያሚያወርዱ ናቸው::
>
> (ቲርሚዚ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

በተቻለ መጠን በነብዩ (ﷺ) ሰለዋት ማውረድ ይህንን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎ ውስጥ ለማካተት መሞከር::

ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-
"በእኔ ላይ አንድ ሰለዋት ያወረደ አላህ (ሱ.ወ) በእሱ ላይ አስር ሰለዋትን ያወርድለታል::"

(አን ነሳኢ)

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

- እንቀጽ
- ሱራ
- ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መስጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

رَبِّ اجْعَلْنِي مُقِيمَ الصَّلَاةِ وَمِن ذُرِّيَّتِي ۚ رَبَّنَا وَتَقَبَّلْ دُعَاءِ

«ጌታዬ ሆይ! ሰላትን አዘውትሬ የምሰግድ አድርገኝ::
ከዘሮቼም (አድርግ):: ጌታችን ሆይ! ጸሎቴንም ተቀበለኝ፤

(ሱረቱል ኢብራሂም 14:40)

ረመዳን 9

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ሃሪሳ ቢን ወሃብ እንደዘገቡት
የአላህ መልእክተኛ(ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-

"የገነትን ሰዎች ልንግራችሁ?
ደካማ እና የተጨቆኑ ሁሉ፤
የገሀነምን ሰዎች ልንገራችሁ?
ጨካኝ፤ ትዕቢተኛ እና ኩራተኛ ሁሉ"

(ኢብኑ ማጀህ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ሰዎችን ይቅርታ ጠይቅ ወይም
ይቅርታቸውን ተቀበል። በእነርሱም
ስም ሰደቃ እና ዱአ አድርግላቸው።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

እንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

اللهم إني أعوذبك من منكرات الأخلق والأعمال والأهواء

**አላህ ሆይ! ከተወገዙ ስነ ምግባሮች ስራዎችና
ፍላጎቶች ባንተ እጠበቃለሁ!**

(ቲርሚዚ)

ረመዳን 10

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

"የወንድሙን ክብር የነካ ሰው ዲናርም ዲርሃምም የሌለበት ጊዜ (ማለትም የትንሣኤ ቀን) ከመምጣቱ በፊት በፊት ይቅርታን ይጠይቅ። መልካም ሥራዎችን የሠራ እንደ ሆነ፤ ከስህተቱ ጋር እኩል የሆ ክፍል ይቀነሳል። በጎ ሥራ ባይኖረው ግን በዚያው ልክ የበደለውን ሰው ክፉ ሥራ ይሸከማል።"

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

የበደላችሁትን ይቅርታ ጠይቁ።
ካልቻላችሁ በነሱ ምትክ ምጽዋትን
ስጡ እና ለነሱም ዱዓ አድርጉላቸው።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

አንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መስጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

رَّبِّ أَدْخِلْنِي مُدْخَلَ صِدْقٍ وَأَخْرِجْنِي مُخْرَجَ صِدْقٍ وَاجْعَل لِّي مِن لَّدُنكَ سُلْطَانًا نَّصِيرًا

ጌታዬ ሆይ! የተወደደን ማግባት አግባኝ። የተወደደንም ማውጣት አውጣኝ። ለእኔም ከአንተ ዘንድ የተረዳን ስልጣን አድርግልኝ።

(ሱረቱል ኢስራእ 17:80)



የአላህ መልእክተኛ(ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-

“ጌታችን በየሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ ወይም 1/3
ውስጥ ወደ ዝቅተኛው ሰማይ ይወርዳል እና እንዲህ ይላል:-
እመልስለት ዘንድ የሚጠራኝ ማነው? እሰጠው ዘንድ ከእኔ
የሚለምነኝ ማን ነው? ይቅር እለው ዘንድ ይቅርታዬን የሚሻ ማነው?

(ሙስሊም ዘግቦታል)



ረመዳን 11
የዕለቱ ሀዲስ

ቀን | ወር | ቀን

የቅርቢቱ አለም ለአማኝ እስር ቤት ሲኾን ለከሃዲ ደግሞ ገነት ነው::

(ሱነን ኢብኑ ማጃህ)

የዕለቱ ድርጊት

استغفر الله واتوب اليه

ከአላህ መሃርታ አለምናለኹ::
ወደሱም እጸጸታለኹ::

100 ጊዜ ማንበብ:

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


እንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

اللهم إنى أعوذ بك من جهد البلاء ودرك الشقاء وسوء القضاء وشماتة الأعداء

አላህ ሆይ! ከከበደ ጥፋት፣ በእኔ ላይ ከሚደርስ መከራ፣ ከመጥፎ እጣ ፈንታ እና ከጠላቶቼ ኩራት ባንተ እጠበቃለሁ::

ረመዳን 12

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ሶፋችሁን እስተካክሉ ተከሻችሁን
አገጣጥሙ በመካከላችሁ ያለውን
ክፍተት ሙሉ ለወንድሞቻችሁ
ለስላሳና ገር ሁኑ ለሸይጣን ቦታን
አትተዉ ሰፉን የሞላ (የቀጠለ) አላህ
ይቀጥለው (አላህ ከረህመቱ ያገጣጥመው)
(አህመድ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

በጀመዓ በህብረት ስገዱ። ሶፋችሁን
(መስመራችኹን) ስታስተካክሉ
ለወንድሞቻችሁ ወይም
ለእህቶቻችሁ ገር ሁኑ።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


አንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

رَبِّ اغْفِرْ وَارْحَمْ وَأَنتَ خَيْرُ الرَّاحِمِينَ

«ጌታዬ ሆይ ማር፤ አዘንም። አንተም ከአዛኞች ሁሉ በላጭ ነህ።»

(ሱረቱል ሙእሚኑን 23:118)

ረመዳን 13

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

የሚሻዕ ሶላት በጀመዓ(በህብረት) የሰገደ ሰው ልክ ግማሽ ለሊት እንደሰገደ ይቆጠርለታል። የፈጅርንም ሶላት በጀመዓ የሰገደ ሰው ለሊቱን ሙሉ እንደሰገደ ይቆጠርለታል።
(ሙስሊም)

የዕለቱ መልካም ተግባር

የፈጅር እና የኢሻእ ሶላትን በጀምዓ መስገድ በተለይም መስጊድ መሄድ።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጂድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

- አንቀጽ
- ሱራ
- ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم أعني على ذكرك وشكرك وحسن عبادتك

አላህ ሆይ! አንተን በማወደስ፣በማመስገንና በመልካሙ በማምለክ ላይ አግዘኝ

(አቡ ዳውድ)

ረመዳን 14

የዕለቱ አንጽቀ

ቀን | ወር | ቀን

ጌታችሁም «ብታመሰግኑ በእርግጥ አጨምርላችኋለሁ ብትክዱም (አቀጣችኋለሁ) ቅጣቴ በእርግጥ ብርቱ ነውና» በማለት ባስታወቀ ጊዜ (አስታውሱ)::

(ሱረቱል ኢብራሂም 14:7)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ለአላህ ምስጋና አቅርቡ በእንደበታችሁ አልሀምዱሊላህ ማለት:: አላህ በሚወደው መንገድ ሀብታችሁን፤ እውቀታችሁንና ጉልበታችሁን ተጠቀሙ::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



አንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

«ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን»

(ሱረቱል በቀራህ 2:201)

ረመዳን 15

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

አንድ ሰው እውቀት ለማግኘት
የሚሄድበትን መንገድ
አላህ ለእሱ የጀነት መንገድን
ቀላል ያደርግለታል።
(ቲርሚዚ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ከቁርኣን አያህ የከፊሉን ተፍሲር አንብብ እና በትርጉሙ ላይ ተደቡር አድርግ (አሰላስል)።

ማንኛውንም የተማሩትን ለቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ያካፍሉ።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


አንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

رَبِّ زِدْنِي عِلْمًا

«ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ»

(ሱረቱል ጣሃ 20:114)

ረመዳን 16

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ባሪያ ይበልጥ ወደ አላህ ቅርብ የሚሆነው በሱጁዱ ወቅት ነው:: (በሱጁድ) ዱዓን አብዙ::
(ሙስሊም ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

አላህ ፊትህ ስትቆሙ ለሰላት ቀደም ብለው ይዘጋጁ:: ዉዱዕ በትክክል አደርጋችሁ ለሰላታችሁ ትኩረት ሰጥታችሁ ስገዱ::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


እንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

اللهم إني أعوذبك من الأربع من علم لا ينفع ومن قلب لا يخشع ومن نفس لاتشبع ومن دعاء لا يسمع

አላህ ሆይ! ከአራት ነገራት ባንተ እጠበቃለሁ:: ከማይጠቅም እውቀት፤ከማይፈራህ ልብ፤ከማትጠግብ ነብስ፤ ከማይሰማ ዱዓ(በአንተ እጠበቃለሁ:: (አቡ ዳውድ)

ረመዳን 17

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

በየቀኑ ሁለት መላኢኮች ከሰማይ ይወርዳሉ ከመካከላቸው አንዱ "አላህ ሆይ! ለለገሰ ሰው ምትክን ስጠው" ሌላውም(መልአክ) "አላህ ሆይ! የከለከለውን ኪሳራ ስጠው"ይላል::

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ለጾመኞች ምግቦችን ማዘጋጀት ካልተቻለ አንድ ብርጭቆ ውሃ እንኳ ብትሆን ማቅረብ::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



አንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم إنى أسألك علما نافعا ورزقا ظيبا وعملا متقبل

አላህ ሆይ! ጠቃሚ የሆነን እውቀት! ጥሩ የሆነን ሲሳይ አንተ ዘንድ ቅቡል የሆነን ስነ ምግባርን እለምንሃለሁ::

(ሱነን ኢብን ማጀህ)

ረመዳን 18

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

"የሞተ ሰው ወደ መቃብሩ ሲወሰድ ሦስቱ ይከተሉታል። (ከተቀበረ በኋላ) ሁለቱ ይመለሳሉ አንዱ ከእርሱ ጋር ይቆያል። ዘመዶቹ፣ ንብረቱ እና ሥራው ይከተሉታል። ዘመዶቹ እና ንብረቱ ሲመለሱ ስራው ከሱ ጋር ይቆያል።"

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ከዚህ በታች ያለውን ዲዓ ለቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ያካፍሉ። በየቀኑ እንዲ ያነቡትም ያበረታቷቸው።

"አንድን (ጠቃሚ) እውቀትን ለሌላው ያስተማረ ሰው በዛ ዕውቀት የሰራው ሰው ምንዳ ይኖረዋል። ይህ ምንዳውን ምንም ሳያጎድል ነው።"

(ሱነን ኢብኑ ማጀህ)

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጂድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት እዝካር
- የምሽት እዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት እዝካር

የዕለቱ ዲዓ፦

يا مقلب قلوب ثبت قلبي على دينك

ልቦችን የምትገለባብጥ (ጌታ ሆይ!) ልቤን በመንገድህ ላይ አፅናት! (ቲርሚዚ)

ረመዳን 19

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

"ሀሰተኛ ንግግርንና መጥፎ ስራን ያልተወ ሰው አላህ ምግቡንና መጠጡን መተዉን ብቻ አይፈልግም (ማለትም አላህ ፆሙን አይቀበለውም)"

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

መጥፎ ንግግሮችን ያስወግዱ በጽሑፎችም ይሁን በቃል (በምላስ)::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



እንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

رَبَّنَا ظَلَمْنَا أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ لَنَا وَتَرْحَمْنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ الْخَاسِرِينَ

«ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን:: ለእኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንኾናለን»

(ሱረቱል አዕራፍ 7:23)

የለይለተል ቀድር ትሩፋት

እኛ (ቁርኣኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው::

መወሰኛይቱም ሌሊተ ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ?

መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት::

በርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ::

እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም ብቻ ናት::

(ሱረቱል ቀድር 1-5)

አቡ ሁረይራ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት:- የአላህ መልዕክተኛ(ﷺ) እንዲህ ብለዋል::

«ረመዳንን ምንዳ ከአላህ እንደሚያገኝ አምኖ የቆመ
ያለፈ ወንጀሉ ይማርለታል::»

አኢሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

"የአላህ መልዕክተኛ(ﷺ) ሆይ! ለይለቱል ቀድር
የትኛዋ ለሊት እንደሆነች ባውቅ ምንድነው ማለት ያለብኝ?"
በማለት ጠየቅኳቸው::

اللهم إنك عفو تحب العفو فاعف عنا

«አላህ ሆይ! አንተ ይቅር ባይ ነህ::
ይቅርታንም ትወዳለህ:: ይቅር በለኝ፤ በይ::" አሉኝ

(ቲርሚዚ)

ረመዳን 20

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

የረመዳን የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ሲጀምሩ ነብየ(ﷺ) ሌሊቱን (በዒባዳ) ያነጉ፤ ወገባቸውን ያጠነክሩና ቤተሰቦቻቸውን (ለመስገድ) ያነቁ ነበር።

(ሱነን ኢብኑ ማጃህ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ለቂያም(ሰላት)፤ ቁርኣን ለመቅራት፤ ለዲዓ እና እዝካር የሚወዷቸውን ሰዎች እንዲቀላቀሉዎት ይጋብዙ።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

እንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት እዝካር
- የምሽት እዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መስጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት እዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم إنك عفو تحب العفو فاعف عنا

አላህ ሆይ! አንተ ይቅር ባይ ነህ፤
ይቅር ባይንትንም ትወዳለህ ይቅር በለን።

(ኢብኑ ማጃህ)

ረመዳን 21

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

በቀድር ለሊት ከአላህ ምንዳን በመሻት አምልኮ የፈጸመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ በሙሉ ይማርለታል። የረመዳንን ወር በተሟላ ኒያ እና ከአላህ ምንዳን በመሻት የጾመ ሰው ከኣላህ ከፍ ያለ ምንዳ ይቸረዋል። ያለፈ ኃጢያቱም ይማርለታል።

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ከመተኛትዎ በፊት ሱራ አል ሙልክን ያንብቡ።

"በቁርኣን ውስጥ አንድ ሱራ አለች። ሠላሳ አያት የያዘች። አንድ ሰው ኃጢአቱን ሙሉ ምታስምረው ።"
አሏም...

"ያ ንግሥና በእጁ የኾነው አምላክ ችሮታው በዛ። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው" ምትለው (ሱራ አል-ሙልክ) ናት።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

እንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

فَاطِرَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ أَنتَ وَلِيِّي فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ ۖ تَوَفَّنِي مُسْلِمًا وَأَلْحِقْنِي بِالصَّالِحِينَ

የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አንተ በቅርቢቱና በመጪረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ። ሙስሊም ሆኘ ግደለኝ። በመልካሞቹም አስጠጋኝ» (አለ)።

(ሱረቱል ዩሱፍ 12:101)

ረመዳን 22

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ከእናንተ መካከል ምርጡ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረው ነው::

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

የሱረቱል ፈለቅ ትርጉም ተማሩና አስተምሩ ወይም ለሌሎች ሰዎች ሼር አድርጉት::

ከመጥፎ ነገር ለመጠበቅ በየቀኑ ሱረቱል ፈለቅን ያንብቡ::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጂድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

አንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ الْفَلَقِ ۝ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ۝ وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ۝
وَمِن شَرِّ النَّفَّاثَاتِ فِي الْعُقَدِ ۝ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ

በል «በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ:: «ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት:: «ከሌሊትም ክፋት ባጨለመ ጊዜ፤ «በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከኾኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት:: «ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ፤ (እጠበቃለሁ በል)::»

(ሱረቱል ፈለቅ 113:1-5)

ረመዳን 23

የዕለቱ አንቅጽ

ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፦ እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ አቀበለዋለሁ። ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና።

(ሱረቱል በቀራህ 2:186)

ቀን | ወር | ቀን

የዕለቱ መልካም ተግባር

በአላህ ስሞች ዲዓ ስለማድረግ...

ታላቅና ታጋሽ ከሆነው አላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። የታላቁ ዐርሽ ጌታ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። የሰማያት ጌታ፣ የምድር ጌታ፣ የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



አንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መስጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዲዓ፦

رب اغفرلى وتب على إنك أنت التواب الغفور

ጌታዬ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ ወደ አንተ መመለሴን ተቀበለኝ። አንተ በጣም መሃሪና መመለስን ተቀባይ ጌታ ነህና!

(ቲርሚዚ)

ረመዳን 24

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

“በጀመዓ የሚሰገደው ሰላት (በግል ከሚሰገደው ሰላት) ምንዳው በ27 ደረጃ የላቀ ነው::”

(ቡኻሪ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

የፈርድ ሰላቶችን በጀምዓ ይስገዱ በተለይም ወደ መስጂድ በመሄድ::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



እንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم إني أسألك موجبات رحمتك وعزائم مغفرتك والسلامة من كل إثم والغنيمة من كل بر والفوز بالجنة والنجاة من النار

"አላህ ሆይ! እዝነትህን የሚያመጣልኝን፣ የማህርታህን ሰበብ፣ ከወንጀሎች ሁሉ መጠበቅን፣ ከመልካም ስራ መጠቀምን፣ የጀነት ስኬትን እና ከጀሐነም እሳት መጠበቅን አለምንሃለሁ" (ሐኪም ዘግበውታል)

ረመዳን 25

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

“ዝምድናን የሚቆርጥ ሰው ጀነት አይገባም::”
(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

ወላጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ እህቶቻችሁንና ዘመዶቻችሁን ጠይቁ ይህን ካልቻላችሁ ደውሉላቸው አሊያም መልእክት ላኩላቸው::

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


አንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስተግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

اللهم الف بين قلوبنا وأصلح ذات بيننا واهدنا سبل السلام ونجنا من الظلمات إلى النور

አላህ ሆይ! ልቦቻችንን አንድ አድርግልን! በመካከላችን ግንኙነታችንን አሳምርልን የሰላም መንገዶችን ምራን! ከፅልመትም ወደ ብርሃን አውጣን!
(አቡ ዳውድ)

ረመዳን 26

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

ከአላህ ጋር መገናኘትን የወደደ አላህም ከእሱ ጋር መገናኘትን ይወዳል። ከአላህ መገናኘትን ያልወደደ አላህም ከእሱ ጋር መገናኘት አይወድም።

(ቡኻሪ ዘግቦታል)

የዕለቱ መልካም ተግባር

በረመዳንም ሆነ ከረመዳን በኋላ ለማቆም የሚያስቡትን ክፉ ልማድ በዝርዝር ይጻፉ ከአላህም ምህረትን ይለምኑ።

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ



እንቀጽ



ሱራ



ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم إنك أعوذبك أن أشرك بك وأنا أعلم وأستغفرك لما لاأعلم

አላህ ሆይ! የማውቅ ሆኜ ሳለሁ ባንተ ከማጋራት ባንተ እጠበቃለሁ! ከማላውቀውም ነገር ባንተ እጠበቃለሁ!

ረመዳን 27

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

سبحان اللهٰ وبحمده

ጠዋትና ማታ 100 ጊዜ
ያለ ሰው በትንሳኤ ዕለት
ማንም ሰው አይበልጠውም
ከእሱ በላይ ያለ ቢሆን እንጂ።
(ሙስሊም)

የዕለቱ መልካም ተግባር:-

سبحان اللهٰ وبحمده

አላህ ከጉድለት ሁሉ የፀዳ ነው።
ምስጋናም ሁሉ ለእርሱ ይገባዋል።

100 ጊዜ

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

አንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት እዝካር
- የምሽት እዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መስጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት እዝካር

የዕለቱ ዱዓ:-

رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

«ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጪዪቱም
አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን»

(ሱረቱል በቀራህ 2:201)

ረመዳን 28

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

አንድ ባሪያ ወንጀል ሲሰራ ጥቁር ነጥብ በልቡ ላይ ታርፋለች። ተጸጽቶና መሃርታን ፈልጎ ከወንጀሉ በተመለሰ ጊዜ ልቡ አብረቅራቂ ሆኖ ዳግም ይጸዳል።
(ቲርሚዚ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

1. ወንጀል ከመስራት መቆጠብ (መራቅ)
2. አላህን ምህረት መለመን
3. ተውበት ማድረግ (መጸጸት)
   ጥፋት ላለመስራት ማቀድ

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


አንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم رحمتك أرجو فلا تكلنى إلى نفسى طرفة عين أصلح لى شأنى كله لا إله إلا أنت

አላህ ሆይ! እዝነትህን እከጅላለሁ! ለአፍታ እንኳን ለነፍሴ አትተወኝ! ጉዳዬን ሁሉ አስተካክልልኝ ካንተ ውጪ በሀቅ የሚመለክ አምላክ የለም!

(አህመድና አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

ረመዳን 29

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

የመጨረሻው ቃል

لا إله إلا الله

የሆነ ጀነት ገባ።

(አቡ ዳውድ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

لا إله إلا الله

ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

100 ጊዜ ማንበብ

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ

እንቀጽ

ሱራ

ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

رَبَّنَا لَا تُزِغْ قُلُوبَنَا بَعْدَ إِذْ هَدَيْتَنَا وَهَبْ لَنَا مِن لَّدُنكَ رَحْمَةً ۚ إِنَّكَ أَنتَ الْوَهَّابُ

"ጌታችን ሆይ! ቅኑን መንገድ ከመራኸን በኋላ ልባችንን አታዘንብልብን። ከአንተ ዘንድ የሆነ ችሮታም ለኛ ስጠን። አንተ በጣም ለጋስ ነህና!"

(ሱረቱል ኢምራን 3:8)

ረመዳን 28

የዕለቱ ሐዲስ

ቀን | ወር | ቀን

አንድ ባሪያ ወንጀል ሲሰራ ጥቁር ነጥብ በልቡ ላይ ታርፋለች። ተጸጽቶና መሃርታን ፈልጎ ከወንጀሉ በተመለሰ ጊዜ ልቡ አብረቅራቂ ሆኖ ዳግም ይጸዳል።
(ቲርሚዚ)

የዕለቱ መልካም ተግባር

1. ወንጀል ከመስራት መቆጠብ (መራቅ)
2. አላህን ምህረት መለመን
3. ተውበት ማድረግ (መጸጸት) ጥፋት ላለመስራት ማቀድ

የሶላት መከታተያ

ፈጅር	ሱናህ
ዙህር	ሱናህ
አስር	ሱናህ
መግሪብ	ሱናህ
ኢሻእ	ሱናህ
ተራዊህ	ዊትር
ታህጁድ	ዱሓ

የቁርአን መከታተያ


አንቀጽ


ሱራ


ጁዝ

ዕለታዊ ማረጋገጫ

- የጠዋት አዝካር
- የምሽት አዝካር
- ኢስቲግፋር (70 ጊዜ)
- ምስጋና
- ሰደቃ መሰጠት
- የደግነት ተግባር
- ቁርአንን ማንበብና ማስተንተን
- የዕለቱ ክዋኔ
- ከእንቅልፍ በፊት አዝካር

የዕለቱ ዱዓ፦

اللهم رحمتك أرجو فلا تكلني إلى نفسي طرفة عين أصلح لي شأني كله لا إله إلا أنت

አላህ ሆይ! እዝነትህን እከጅላለሁ! ለአፍታ እንኳን ለነፍሴ አትተወኝ! ጉዳዬን ሁሉ አስተካክልልኝ ካንተ ውጪ በሀቅ የሚመለክ አምላክ የለም!

(አህመድና አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

የኔ ዱዓ



የዘውትር የደግነት ተግባር ምሳሌ፦

- ፈገግ ማለት
- ይቅርታ ማደርግ
- ለምታገኟቸው ሰዎች ሰላምታ ማቅረብ
- ከሀሜት መታቀብ (መራቅ)
- ለተቸገሩ ገንዘብ መለገስ
- ሰዎችን በደግነትህ አስደምም (አስገርመው)
- ቁጣህን እና ምላስን መቆጣጠር
- ለሌሎች ሰዎች ዱዓ ማደረግ
- ከመንገድ ላይ ቆሻሻ ማስወገድ
- ዱዓ ስናደርግ ለሌላ የቤተሰብ አባላትም ዱዓ ማደረግ
- ለአለዋፋት ወይም ለሌሎች እንስሳት የተወሰነ ምግብና ውሃ መስጠት
- የቤት ውስጥ ሥራዎችን ማገዝ (መርዳት)
- ሰዎችን በሚፈልጉት ነገር መርዳት/ማገዝ
- ጥሩ ነገር መናገር ለዘመድ አዝማድ መደወል ወይም መልእክት መላክ
- ለጾሙ ሰዎች መጠጥና ምግብ ማዘጋጀት

ከእንቅልፍ በፊት የሚባል ዚክር

سبحان الله الحمدلله الله أكبر

ጥራት ለአላህ የተገባ ነው:: (33×)	ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው:: (33×)	አላህ ትልቅ ነው:: (33×)

አያቱል ቁርሲይን (አልበቀራህ 255)፤ ሱረቱል ኢኽላስ (3×)፤ ሱረቱል ፈለቅ (3×)፤ ሱረቱል ናስ (3×) ማንበብ::

ሱረቱል በቀራህን 285 - 286 ማንበብ::

آمَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ ۚ كُلٌّ آمَنَ بِاللَّهِ
وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ ۚ وَقَالُوا
سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا ۖ غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ

لَا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا ۚ لَهَا مَا كَسَبَتْ وَعَلَيْهَا مَا اكْتَسَبَتْ ۗ
رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَا إِن نَّسِينَا أَوْ أَخْطَأْنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تَحْمِلْ عَلَيْنَا إِصْرًا كَمَا
حَمَلْتَهُ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلْنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِ ۖ وَاعْفُ
عَنَّا وَاغْفِرْ لَنَا وَارْحَمْنَا ۚ أَنتَ مَوْلَانَا فَانصُرْنَا عَلَى الْقَوْمِ الْكَافِرِينَ

መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ:: ምእምኖቹም (አንደዚሁ):: ሁሉም በአላህ፤ በመላዕክቱም፤ በመጻሕፍቱም፤ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ:: «ሰማን፤ ታዘዝንም:: ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን):: መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም::

አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም:: ለርስዋ የሠራችው አላት:: በርስዋም ላይ ያፈራችው (ጎጢአት) አለባት:: (በሉ):- ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን፤ (አትቅጣን):: ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን:: ጌታችን ሆይ! ለኛም በርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን:: ከእኛም ይቅርታ አድርግ ለእኛም ምሕረት አድርግ:: እዘንልንም፤ ዋቢያችን አንተ ነህና:: በከሓዲዎች ሕዝቦች ላይም እርዳን::

(ሱረቱል በቀራህ 285-286)



ከእንቅልፍ በፊት የሚባል ዚክር

بِاسْمِكَ اللَّهُمَّ أَمُوْتُ وَأَحْيَا.

አላህ ሆይ! በስምህ እሞታለሁ፤ ነፍስም እዘራለሁ::

بِاسْمِكَ رَبِّيْ وَضَعْتُ جَنْبِيْ وَبِكَ أَرْفَعُهُ فَإِنْ أَمْسَكْتَ نَفْسِيْ فَارْحَمْهَا وَإِنْ أَرْسَلْتَهَا فَاحْفَظْهَا بِمَا تَحْفَظُ بِهِ عِبَادَكَ الصَّالِحِيْنَ.

ጌታዬ ሆይ! በስምክ ጎኔን አሳርፌያለሁ:: በስምህም አነሳዋለሁ:: ነፍሴን በዚያው ካስቀራሀት እዘንላት:: ከላክካት ደግሞ መልካም ባሮችህን በምትጠብቅበት (ስልትህ) ጠብቃት::

(ቡኻሪ ዘገቦታል)

اَللَّهُمَّ إِنَّكَ خَلَقْتَ نَفْسِيْ وَأَنْتَ تَوَفَّاهَا لَكَ مَمَاتُهَا وَمَحْيَاهَا إِنْ أَحْيَيْتَهَا فَاحْفَظْهَا وَإِنْ أَمَتَّهَا فَاغْفِرْ لَهَا. اَللَّهُمَّ إِنِّيْ أَسْأَلُكَ الْعَافِيَةَ.

አላህ ሆይ! ነፍሴን ፈጥረሃታል:: የምትገድላትም አንተው ነህ:: ሞቷም ህይወቷም ላንተ ነው:: ህያው ካደረግካት ጠብቃት:: ከገደልካት ደግሞ ምህረትህን ለግሳት:: አላህ ሆይ! ጤንነትን እጠይቅሃለው::

(ሙስሊም ዘገቦታል)

اَللَّهُمَّ قِنِيْ عَذَابَكَ يَوْمَ تَبْعَثُ عِبَادَكَ.

አላህ ሆይ! ባሮችህን በ ሞት ቀስቅስበት ወቅት ከቅጣትህ ጠብቀኝ::





ጥረታችንን እና መልካም ሥራችንን
አላህ ይቀበለን! የሠራነውንም
ጥፋት ይቅር ይበለን::

አሚን!